5.2.1/98/4

08 ህዳር 2004

ለኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ለአፍሪካ ኢንሹራንስ

ለአዋሽ ኢንሹራንስ

ለኢትዮ ላይፍ ኢንሹራንስ

ለግሎባል ኢንሹራንስ

ለአንበሳ ኢንሹራንስ

ለንብ ኢንሹራንስ

ለናይስ ኢንሹራንስ

ለናይል ኢንሹራንስ

ለኒያላ ኢንሹራንስ

ለኦሮሚያ ኢንሹራንስ

ለህብረት ኢንሹራንስ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፦ <u>የመመሪያ ቁጥር 52/2003 ማሪሚያን ይመለከታል</u>

ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎች የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 52/2003 በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ሆኖም የመመሪያው አንዳንድ አንቀፆች የተሻሻሉ ስለሆነ የተሻሻለውን መመሪያ 3 ገፅ ኮፒ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia
Ethiopian Revenues and Customs Authority

1·0/75/3
3 0 ጥቅምት 2004

ለአ/አ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአ/አ የንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
ለሚሌ ቅ/ጽ/ቤት
ለባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት
ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት
ለጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት
ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት
ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት
ለሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት
ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመመሪያ ማሻሻያ ስለመላክ</u>

ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ ገብተው ጉዳት በደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች ላይ ስለሚታሰበው ቀረጥና ታክስ የወጣው መመሪያ ቁጥር 52/2003 የተሻሻለ ስለሆነ ከዚህ ጋር በተላከው ማሻሻያ መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

መላኩ ፈንታ
ዋና ዳይሬክተር
30/02/04

<u>ግልባጭ</u>፣

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
  <u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>
- ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
  <u>አዲስ አበባ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY


ቁጥር 5/2/1/82/3
Ref. No:
ቀን 17 ጥቅምት 2004
Date

ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ጉዳዩ፣ የመመሪያ ቁጥር 52/2003 ማሻሻያን ይመለከታል

ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ ገብተው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎች የቀረጥና ታክስ አከፋፈል ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 52/2003 በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ሆኖም መመሪያው የዲፕሎማቲክ መብት ባላቸው አለም አቀፍ ድርጅቶችና ሠራተኞቻቸው እንዲሁም ሌሎች በመንግሥት ስምምነት ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ መብት ያገኙ ድርጅቶች መብታቸውን እንደሚያጣብብ በመግለፃቸው ምክንያትና መነሻ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር መመሪያው እንዲሻሻል ጠይቋል።

የጥያቄውን አግባብነትና የመመሪያው መሻሻል አስፈላጊነት በመቀበል የመመሪያውን ማሻሻያ አዘጋጅተን እንዲፀድቅ አቅርበናል።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣

☞ ለዐቃቤ ህግ ዳይሬክቶሬት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!


ቴ / Tel. 011 662 98 00
/ Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

<u>የመመሪያ ቁጥር 52/2003 ማሻሻያ</u>

መሪያ ቁጥር 52/2003 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

/ የመመሪያው አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ንዑስ አንቀፅ (2) እንዲሻሻል እና አዲስ ንዑስ አንቀፅ (3) እንዲጨመር ተደርጐ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባው ተሽከርካሪ፤

ሀ. የኤምባሲዎችና ሠራተኞቻቸው እንዲሁም በዚሁ አግባብ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶችና ሠራተኞች፤

ለ. የዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው፤

ሐ. መንግሥታዊ፣ ለለም አቀፋዊ ወይም ለህጉራዊ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው፤

መ. ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በተደረገ ስምምነት ከቀረጥ ነፃ ተሽከርካሪ ወደ አገር እንዲያስገቡ በተፈቀደላቸው ሰዎች አማካኝነት የገባ ከሆነ፤ ወይም

ሠ. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር የገባው ተሽከርካሪ የአገልግሎት ዘመኑን የጨረሰ ከሆነ፣

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ አይሆንባቸውም፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ከሀ እስከ መ በተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው ከጉዳቱ የተረፈውን ዕቃ ዋጋ መሠረት በማድረግ ቀረጥና ታክሱ ተሰልቶ ዕቃው ከመተላለፉ በፊት ቀረጥና ታክሱ ይሰበሰባል፡፡

፭/ የመመሪያው አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1፣2 እና 3 ተሰርዞ በሚከተለው አንቀፅ 5 ተተክቷል፡፡

5) <u>የመድን ሰጪው ሌሎች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም መድን ሰጪ ከፍተኛ ጉዳት ስደረሰበት ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ለገባ ተሽከርካሪ ለባለመብቱ የሚከፈለውን የኢንሹራንስ ገንዘብ ከመክፈሉ በፊት ባለሥልጣኑ በተሽከርካሪው ላይ ባለው የቀደምትነት መብት መሠረት የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ መክፈል አለበት::

፭/ የመመሪያው አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ (1) ተሰርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀፅ (1) ተተክቷል::

15(1) የመድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ ስሌት በተመለከተ ተሽከርካሪው አገር ወስጥ ሲገባ ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ መሠረት በማድረግ ተሽከርካሪው ጉዳት እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ በየዓመቱ የአገልግሎት ቅናሽ በማድረግ ይሆናል::"

አዲስ አበባ ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር